39. <u>የእርጅና ቅናሽ መጣኔዎች</u>

1/ ዋጋው በሚቀንስ ሀብት ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የእርጅና ቅናሽ መጣኔ በሚከተሉት ምድቦች እና ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ተፈፃሚ ይደረጋል፤

| ዋጋው የሚቀንስ ሀብት | የቀጥተኛ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መጣኔ | ዋጋው እየቀነሰ የሚሄድ የእርጅና ቅናሽ ዘዴ መጣኔ |
|---|---|---|
| ኮምፒውተር፣ሶፍትዌር እና የመረጃ ማከማቻ መሣሪያ | 20 በመቶ | 25 በመቶ |
| ግሬንሀውስ | 10 በመቶ | - |
| ግሬንሀውስን ሳይጨምር በማይንቀሳቀስ ሀብት ላይ የሚደረግ ማሻሻያ | 5 በመቶ | - |
| ሌላ ማንኛውም ዋጋው የሚቀንስ ሀብት | 15 በመቶ | 20 በመቶ |
| ለማዕድን እና ነዳጅ የልማት ሥራዎች ጥቅም ላይ የሚውል ዋጋው የሚቀንስ ሀብት | 25 በመቶ | 30 በመቶ |

2/ ግዙፋዊ ህልዎት ለሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች ተፈጻሚ የሚሆነው የእርጅና ቅናሽ መጣኔ፣

ሀ) የንግድ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የተደረገ ወጪ 25 በመቶ፣

ለ) በፊደል ተራ (ሀ) ከተመለከተው ውጪ ለሆነ ከ10 ዓመት በላይ ለሚያገለግል ግዙፋዊ ህልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት 10 በመቶ፣ ወይም

ሐ) ለሌላ ማንኛውም ግዙፋዊ ህልዎት የሌለው የንግድ ሥራ ሀብት 100 በመቶን ግዙፋዊ ህልዎት ለሌለው ሀብት የአገልግሎት ዘመን በማካፈል የሚገኘው መጣኔ፣

ይሆናል፡፡

3/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "የንግድ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የተደረገ ወጪ" ማለት ግብር ከፋዩ የንግድ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሚያወጣው በአዋጁ አንቀጽ 25(7)(ሀ) ለ"ግዙፋዊ ህልዎት የሌላቸው የንግድ ሥራ ሀብቶች" በተሰጠው ትርጉም ተራ ቁጥር (4) የተመለከተው ወጪ ነው፡፡



Ico.Tx Regulation WG?